በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኤፕሪል 21-30 እና ከሜይ 1-10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2024
አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ - 1 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 2 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 2 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ.- 5 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2024 - 8 -
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር - 8 -
ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2024 - 8 -
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -
እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 9 -
ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10፣ 2024 - 9 -
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 9 -
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 10 -
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 10 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት አስር ቀናት በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ እና በደቡብ እንዲሁም በደቡብ በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋንና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአይሻ 113.0፣ በሞያሌ 76፣ በማጂ 71.5፣ 29.7፣ በሸላቦ 61.0፣ 47.5 በዶሎ 58.2፣ በአዋሽ አርባ 57.5፤ በሚሌ 54.0፣ በካራሚሊ 53.8፣ 33.9፣ 24.6፣ በኮምቦልቻ 52.3 እና 26.3 በኮንሶ 47.6፣ 22.2 በወረኢሉ 43.0፣ በተርጫ 31.9፣ በቁሉቢ 38.6፣ 36.8፤ በቡሌሆራ 36.3፣ በሀዋሳ 32.3፣ በላንጌ 32፣ በአዋሬ 31፣ በዲላ 20.8፣ 30.5፣ በቦሬ 28.7፣ በጭራ 28.6፣ በጨለንቆ 28.4፣ በሰመራ 28.2፣ በነግሌ 28፣ በሳዉላ 27.6፣ በደራሮ 27.6፣ በጂንካ 23.7፣ 22.4፣ 27.4፣ ፣ በቴፒ 25.4፣ 23.2 በጊኒር 23.5፣ በጭናቅሰን 23.4፣ በቡኢ 23፣ በቡርጂ 22.4፣ በደብረብርሃን 21.7፣ በወላይታ ሶዶ 21.7፣ በአርባምንጭ 21.5፣ በምዕራብ አባያ 21፣ 21 በእነዋሪ 20.7 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ ፤ ከአማራ ክልል ደቡብ ወሎ፣ የሱማሌ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፤ የየም ልዩ ዞን፣ ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከ21-150 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-9 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ሁሉም የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ወሎ፣ ምስራቅ ጎጃም፤ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ) እና ደቡብ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ ባሌ፣ አዲስ አበባ፣ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬ ዳዋ ላይ ከ2-20 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ደቡብ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ቡኖ በደሌ፤ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አዲስ አበባ፣ እንዲሁም  ሀረሪ እና ድሬ ዳዋ፤ ከአማራ ክልል ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል  ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤  ከአፋር ክልል ዞኖች ኦን 1፣ 4፣3 እና 5 ዞኖች፤ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066   ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ዳርቻዎች በሚገኙ አካባቢዎች የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-43.8 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 1)። ባለፉት አስር ቀናት ከ40 ዲ.ሴ በላይ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በጎዴ፣ በአቦቦ፣ በአዋሽ አርባ፣ በዱብቲ፣ በፉኚዶ፣ በጋምቤላ፣ በገዋኔ፣ በላሬ በመተማ፣ እንዲሁም በሰመራ ከሌሎቹ ቆላማ አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር በመጠኑ ከፍተኛ ሲሆን፣ ለተከታታይ ቀናት ከ40 እስከ 43.8 ዲ.ሴ የሚደርስ የሙቀት መጠን ተመዝግቧል (ምስል 1) ።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et







ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት የበልግ አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት በመካሄድ ላይ ላለው የእርሻ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን ቀደም ብለው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ከኤፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ የመኸር ወቅት ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ በሌላም በኩል በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት የነበረ ሲሆን ይህም ሁኔታ እርጥበት አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነበር፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በባሮአኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት መካከለኛው እና የታችኛው አዋሽ፣ መካከለኛ ምስራቅ አባይ፣ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ እና አፋር ደናከል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት የታችኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ፣ ኦጋዴን፣ የላይኛው አባይ እና አብዛኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ በጠተናከረ ሁኔታ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጋር ተያይዞ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው ።


በመጪዎቹ የኤፕሪል ሶስተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ይበልጥ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉና በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በደቡባዊው አጋማሽ፤ በመካከለኛው እና በምስራቅ  የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በደቡብ ምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምስራቅ፣ መካከለኛው፤ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቅጸበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል  ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፤ ቦረና፤ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፤ የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚያዳርስ የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፤




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066    ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ከአማራ ክልል የደቡብ ጎንደር ዞን፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የዋግህምራ ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ክልል የአሶሳ፣ የማኦኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)። በተጨማሪም በአፋር ክልል፤ ሀረር፤ ድሬዳዎ፤ ምስራቅ ሸዋ፤ የሶማሌ ክልል ዞኖች፤ አዲስ አበባ እና በምስራቅ አማራ አከባቢዎች ከሚኖረው ተደጋጋሚነት ያለው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በመነሳት ቅጸበታዊ ጎርፍ የማስከተል አቅም ስለሚኖረው ከወዲሁ ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ያሳስባል (ካርታ 6 እና 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃር




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሜይ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም በልግ ዋናኛ ሁለተኛ  የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 9) ።

Rainfall performance (mm) for 1-10 May 2024




ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10፣ 2024

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የመኸር ሰብሎችን ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ ለመዝራት ምቹ ስለሚሆን አርሶ አደሮች የሚገኘውን እርጥበት ለመጠቀም የሚያስችል አስፍላጊውን ግብዓትና ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ሚና ስለሚኖረው በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች በማሳም ሆነ ከማሳ ውጪ የውሃ እቀባ ስራዎችን በማከናወን በየመሀሉ ለሚከሰቱ ደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን ይህም ሁኔታ በተወሰኑ ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ስለሚችል ለዚሁ ችግር ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ጉዳትን ለመቀነስ የሚያሰችል ጥንቃቄ ከማድርግ ጎን ለጎን የሚገኘውን እርጥበት በላቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖር ሲሆን፤ በሌሎች ተፋሰሶች ላ ደግሞ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህም ሁኔታ በየተፋሰሶች የሚገኙት የውሃ አካላት የተሻለ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም ለመስኖም ሆነ ለሀይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ የግድቦችን የውሃ መጠን የሚያሻሽል በመሆኑ፤ ይህንኑ እድል ለመጠቀም የሚያሰችል የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et